ጋዜጣዊ መግለጫ
የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2017/22

ለበለጠ መረጃ 011-130-7033
http://et.usembassy.gov

በአሜሪካ ኤምባሲ 39 አዳዲስ የሰላም ጓዶች ቃለመሐላ ፈጸሙ

አዲስ አበባ፤ መስከረም 5፤2010 ዓ.ም - የአሜሪካ ኤምባሲ የበላይ ጉዳይ ፈጻሚ ትሮይ ፍትሪል በአማራ፤ ትግራይ፤ ኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርነት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሚሰጡ 39 አዳዲስ የሰላም ጓዶች በኤምባሲው ቅጥር ግቢ ቃለ መሐላ አስፈጽመዋል። ይህም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በጤና፤ ግብርና እና ትምህርት ዘርፎች የተሰማሩትን አሜሪካውያን በጎ ፈቃደኞች ቁጥር 130 ያደርሳል።

በዛሬው ዕለት ቃለ መሐላቸውን የፈጸሙት የሰላም ጓዶች፤ በኢትዮጵያ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትን ማስፋፋት ፕሮገሬ የሆነው (PELLE) ስር የሚሰማሩ የአራተኛው ቡድን አባላት ናቸው። በሚሰማሩባቸው አካባቢዎች በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትንሹ በሦስት ክፍሎች ተመድበው ለ9ኛ ወይም 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣሉ። ቋንቋው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን እንደ ዋነኛ መስፈርት ከማገልገሉም በላይ ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በርካታ የዕድል በሮችን ይከፍታል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻለ ግንኙነት እንዲኖራቸውም ያደርጋል።

በጎ ፈቃደኛ የሰላም ጓዶች በሀገሪቱ አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ባለባቸው አከባቢዎች በመሰማራት፤ በአካባቢው ከሚገኙ መምህራን፤ አስተዳዳሪዎች እና ተሟጋቾች ጋር በሚኖራቸው ትብብር የኅብረተሰቡን ፍላጎት የሚመጥኑ በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ። በትብብር የሚቀረጹ የልማት ሥራዎች፤ ሰፊ የማኅበረሰብ ተሳትፎን በማረጋገጥ የተሻለ እና ዘላቂነት ያለው ውጤት ያስገኛሉ። እንደ ጾታ እኩልነት፤ ትምህርት፤ የወጣቶች የአመራር ተሳትፎ እና ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የመሳሰሉ በርካታ ተግባራት በዚህ ፕሮገሬ ተካተዋል።

አዲሶቹ የሰላም ጓዶች ለበጎ አገልግሎት ሥራቸው የሚያግዝ የሦስት ወራት ስልጠና ተከታትለዋል። በስልጠናቸውም ስለማስተማሪያ ዘዴ፤ ፔዳጎጂ እና በአንድ ጊዜ ከ1,000 በላይ ተማሪዎችን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ክፍለ ጊዜዎች በብቃት ለማስተናገድ የሚያስችላቸውን ክህሎት አዳብረዋል። በተጨማሪም፤ በምድብ ቦታቸው ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት እንዲረዳቸው ለ125 ሰዓታት የአማሪኛ፤ አፋን ኦሮሞ ወይም ትግሪኛ ቋንቋ ስልጠና ወስደዋል። ዛሬ ቃለመሐላ የፈጸሙትን ጨምሮ፤ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ እስካሁን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሰማሩ የሰላም ጓዶች ቁጥር ከ3,600 ይበልጣል።

ስለ ሰላም ጓድ፤- ግንባር ቀደም የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የአገልግሎት ተቋም ሲሆን፤ አሜሪካውያንን ከሀገራቸው ውጭ በመላክ፤ በዓለም ላይ ለሚታዩ አንገብጋቢ የሰው ልጆች ፍላጎቶች የመፍትሔ አካል እንዲሆኑ ያበረታታል። በጎ ፈቃደኛ የሰላም ጓድ አባላት በትምህርት፤ ጤና፤ ምጣኔ ሀብት ልማት፣ ግብርና፤ አካባቢ እና ወጣቶች ልማት ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ማቃለል የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ለመቅረጽ ከአካባቢ አስተዳዳሪዎች፤ ትምህርት ቤቶች፤ የማኅበረሰብ አባላት፤ በአነስተኛ የንግድ ዘርፍ ከተሰማሩና ከሥራ ፈጣሪዎች ጋር በመሆን ይሰራሉ።

###